

የ ደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን

# የዓፄ መስቀል ዘይቤ



ግርማዊ ጃንሆይ በአፄ መስቀል በዓል ላይ
ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጉንጉን አበባ ሲቀበሉ ።

አዲስ አበባ መስከረም ፱ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ· ም

www.ethiopianorthodox.org

# የዓፄ መስቀል ዘይቤ

ይህ መጽሔት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በ፵፭ኛው ዘመነ መንግሥት ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ በሆኑ በሁለተኛው ዓመት መስከረም ፱ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ ም ለሚከበረው የአፄ መስቀል በዓል በተለይ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ የድርሰትና ስብከት ክፍል ዋና መምሪያ ተዘጋጀ ።

**<u>አ ዘ ጋ ጅ</u>**

ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ

አዲስ አበባ መስከረም ፱ ቀን ፲፱፻፷፭ ዓ ም

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ኛ | ተቀጸል ጽጌ (ርእሰ አንቀጽ) . . . . | ፱ |
| ፪ኛ | የቅዱስነታቸው የርእሰ ዓውደ ዓመት መልእክት . . | ፲፩ |
| ፫ኛ | የሰላም ልደት በአፍሪካ . . . . . | ፲፭ |



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

ጽድቅ ሪታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት



ብፁዕ ወቅዱስ ቀዳማዊ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

(ርእሰ አንቀጽ)

# ተቀጸል ጽጌ

ተቀጸል ጽጌ የሚለውን ምሥጢራዊና መንፈሳዊ መዝሙር የጀመረው የዜማና የቅኔ መሥራች የሆነው ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ነው ፤ የመሠረተውም በስድስተኛው መቶኛ ዓመት መጀመሪያ በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት መሆኑን የሃይማኖትና የባህል ሊቃውንት ያስረዳሉ ፤ በዚሁ መሠረት የክረምቱና የልምላሜው ጊዜ አልፎ የአበባውና የፍሬው ጊዜ በሚተካበት በመስከረም ሃያ አምስት ቀን ቅዱስ ያሬድ ወደ አፄ ገብረ መስቀል ቤተ መንግሥት ሂዶ ከንጉሡ ዙፋን ፊት ቀርቦ «ተቀጸል ጽጌ ገብረ መስቀል አፄጌ » በማለት እየዘመረ አሸብሽቧል ። ከዚሁ ሲያያዝ በመጣው ባህልና ሥርዓት የቤተ ክርስቲያን መዘምራን ፤ ቀሳውስትና ዲያቆናት የክህነትና የመዐርግ ልብሳቸውን ለብሰው በመሰለፍና መስቀል ባመያዝ ከቀትር በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ወደ ቤተ መንግሥት ይሄዳሉ ንጉሡ በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጠ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በቀኝ ዕጨጌው በግራ ሲቀመጡ ሌሎችም ሊቃውንትና የታላላቅ አድባራት አለቆች እንደየመዓርጋቸው በቀኝና በግራ ይቀመጣሉ « ተቀጸል ጽጌ አፄጌ » የሚለውን ዜማ መዘምራኑ በሕብረት ይዘምራሉ ፤ የቤተ መንግሥት ሰዎች ልዩ ልዩ ኅብረ መልክዕ ያላቸውና የተጐነጐኑ አበቦች ወደ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ያቀርባሉ ፤ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ አበቦችን በመስቀሉ ባርከ መልኩ ያማረውና መዐዛው የጣፈጠው አበባ ተመርጦ በመጀመሪያ በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ለንጉሡ ከታደለ በኋላ ለሌሎችም እንደየመዐርጋቸው ይታደላል ።

ይህ ዓይነቱ የተቀጸል ጽጌ ስነ ሥርዓት ከአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት እስከ አፄ ዳዊት ዳግማዊ ድረስ በየዓመቱ መስከረም ሃያ አምስት ቀን ሲፈጸም ከኖረ በኋላ ዳግማዊ አፄ ዳዊት የጌታን ግማደ መስቀል ከኢየሩሳሌም አስመጥቶ መስከረም አሥር ቀን ወደ ኢትዮጵያ ባስገባበቅ ጊዜ የአፄ መስቀልና የተቀጸል ጽጌ በዓል በአንድነት መስከረም አሥር ቀን እንዲከበር በሊቃውንት ስለተወሰነ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ባለማቋረጥ ይህ መንፈሳዊ በዓል በቤተ መንግሥትና በቤተ ክህነት በታላቅ ስነ ሥርዓት ሲከበር ኖሯል ወደፊትም ይኖራል ።

የትርጓሜ ሊቃውንት እንደሚሉት ተቀጸል ጽጌ ብዙ ፍችና ምሥጢር አለው ጽጌ ወይም አበባ የሚለው ቃል ራሱ ጸገየ አበበ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ቃል ሲሆን ምሥጢሩ የሚያመለክተው « ጽጌ የተባለ በጽጌ የተመሰለ የንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ነው እግዚአብሔር የንጉሡን ዘመነ መንግሥት እንዲባርክለት ፤ ዘውዱን እንዲቀድስለት በየዓመቱ ክህናቱ ተቀጸል ጽጌ አፄጌ » (ንጉሥ ሆይ ዘውድን ተቀዳጅ) እያሉ ለንጉሡ ይጸልዩለታል በማለት ጥቂቶቹ ሊቃውንት ሲተርኩ ሌሎች ደግሞ በሚሰጡት ሐተታ ጽጌ የተባለች በጽጌ የተመሰለች ሃይማኖት ናት በአራቱ ቤተ መቅደስ ያቋምና በለዝ የሚባሉ ሁለቱ ዓዕማድ በቀኝና በግራ ተተክለው የቅዱስ ጴጥሮስና

www.ethiopianorthodox.org

የቅዱስ ጳውሎስ ምሳሌዎች ሆነው ይኖሩ ነበር ። በሁለቱ ዓዕማድ ራስ ላይ አንዲት አበባ ተቀርጻ ትታይ ነበር እሷም የሃይማኖት ምሳሌ ናት እያሉ ያትታሉ ። የተቀጸል ጽጌ በዓል በሚከበርበት በዚህ ዕለት ካህናቱ የሚናገሩት ቀለም ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ በሃይማኖት እያሉ ክርስቲያኖችን ማፍራታቸውን የሚያወሳና የሁለቱን ብርሃናዊ ተልእኮ በቅልህ የሚያስረዳ በመሆኑ ከሊቃውንት የተሰጠው ምሳሌና ምሥጢር ትክክለኛ እንደሆነ ይታመናል ። «አሕዛብ አስተጋብኡ ጽጌ ረዳ ወሦኩሰ ተርፈ በኃበ አይሁድ ማለት አሕዛብ አበባ ሰበሰቡ እሾሁ ግን በአይሁድ ዘንድ ቀረ » የሚለው ቃል የአሕዛብን ሃይማኖት የአይሁድን ክህደት የሚያመለክት ምሥጢራዊ ቃል መሆኑ በሃይማኖተ አበው መጽሐፍ ተገልጦ ስለተጻፈ ከፍ ብለን እንደገለጽነው ጽጌ የሚለው ቃል ሃይማኖት ተብሎ የሚተረጐም መሆኑ ታምኖበታል ። በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት በየዓመቱ መስከረም አሥር ቀን የክህነት ልብሳቸውን በመልበስ ወደ ቤተ መንግሥት እየሔዱ « ተቀጸል ጽጌ ኃይለ ሥላሴ አፄጌ » የሚለውን መሠረታዊ መዝሙር በመዘመር ሃይማኖትን ተቀዳጅ ዘውዱን ይባ ፡ክ ፡ህ እያሉ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ይዘምራሉ ።

# የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የርዕሰ ዓውደ ዓመት መልእክት

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

## ዓመተ እግዚአብሔር ዓመተ ምሕረት

ልዑል እግዚአብሔር የሰው ልጅ ሊገለገልባቸው ካዘጋጃቸው ብዙዎች የሥነ ፍጥረት ድርጅቶች አንዱ ጊዜ ነው ። ጊዜ የጨለማና የብርሃን ክፍሎች አሉት ፤ ሰው ሥጋዊ ሥራውን በክፍለ ብርሃን ጊዜ ይሠራል ፤ በክፍለ ጽልመት ጊዜ ያርፋል ።

በመንፈሳዊ ሕይወቱ ግን መሪ ብርሃኑ እግዚአብሔር ስለሆነ ጨለማና ብርሃን አይፈልፈረቁበትም ፤ «በደስታዬ በአንተ ዘንድ ሌሊትም እንደ ቀን ብርሃን ነው ፤ ሀገሪቱ ፀሐይና ጨረቃ እንዲያበሩላት አትሻም እግዚአብሔር ያበራላታልና በጉ ማለት ሰው ሆኖ የተቤዠት አምላክም መብራቷ ነውና ሌሊት የለባትምና በመዓልትም በሌሊትም በሮቿ አይዘጉም ፤ እንግዲህ ሌሊት የለም ሰዎችም የሻማ ብርሃን ወይም የፀሐይ ብርሃን አይሹም ፤ እግዚአብሔር ያበራላቸዋልና » ተብሎ ተጽፏል ። ስለዚህም አእምሮ ያለው ሰው በመዓልትም በሌሊትም መንፈሳዊ ሥራውን ከማከናወን አይገታም ። በቤተ ክርስቲያን እንደ የሥርዓቱ እንደየድርጅቱ የሰዓታት ፤ የመዝሙር ፤ የማኅሌት ፤ የቅዳሴ አገልግሎት በመዓልትም በሌሊትም ይፈጸማል ። እግዚአብሔርና ምእመናኑ ለሚያደርጉት ግንኙነት የቤተ ክርስቲያን በሮች በመዓልትም በሌሊትም በሥርዓት ክፍት ናቸው ፤ እንዲህ ሲሆን ሰው ከሥጋና ከነፍስ ከሁለቱ አንዱ የሆነ ፍጡር በመሆኑ ሰዓት መጥኖ ጊዜ ወስኖ መሥራት ለሕይወቱ መመሪያ ሆኖ የተሰጠው ነገር ነው ። ስለዚህም ቅጽበትን በደቂቃ ፤ ደቂቃን በሰዓት ፤ ሰዓትን በመዓልትና በሌሊት መዓልትና ሌሊትን በዕለት ፤ ዕለትን በወር ፤ ወርን በዓመት እያጠቃለለ ሥራውን ያከናውናል ። የሕይወት ጉዞውን ይጓዛል ፤ ሰዓታት ፤ ዕለታት ፤ አውራህ የሚጠቃለሉበት የጊዜ መስፈሪያ ዓመት ስለሆነ አጠቃሎ ክብ ዙረያውን የሚጀመርበት ቀን « ርእሰ ዓውደ ዓመት » መባቻ ፤ የዘመን መለወጫ ይባላል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ልዑል እግዚአብሔር በዚሁ ዓመት እንዲፈጸሙ የመደባቸው ሥራዎች ለሚከናወኑበት ዓመተ እግዚአብሔር ዓመተ ምሕረት ይባላል ። በተለይም ይህ ቃል ዘመነ ሥጋዌን የሚመለከት ቢሆንም « ጊዜ ገቢር ለግዚአብሔር » ለእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ አለው ፤ ተብሎ የተመለከተውን መደብ ሳይለቅ ነው ፤ የእግዚአብሔር ዓመት ብለን ስንናገር እግዚአብሔር የተወሰነ ዘመን ኖሮ ያልፋል ፤ በተወሰነ ዘመን ሠርቶ ያርፋል ፤ በተወሰነ ጊዜ ነግሦ ይሻራል አይባልም የሚባል አይደለም ። ዘለዓለም ኗሪ ፤ ዘለዓለም ሠራተኛ ፤ ዘለዓለም ንጉሥ ነው ፤ የእግዚአብሔር ዓመት ተብሎ መጠራቱ ፍጥረት ለተወሰነ ዘመን ኖሮ በተወሰነ ዘመን ሠርቶ የሚያልፍ ሲሆን ዘለዓለም ኗሪ አምላክ በየጊዜው ለሚነሣው ፍጥረት በየጊዜው የሚያደ



www.ethiopianorthodox.org

ርግለትን የከሀሊነቱን የቸርነቱን የጌትነቱን ሥራ ለመግለጽ ነው ፤ ዛሬ የጨረስነውን ዓመት መለስ ብለን በዓይነ ሕሊና ብንመለከት በዓመቱ ውስጥ እግዚአብሔር የፈጸመልን ሥራ ብዙ ነበርና ፣ ዓመተ እግዚአብሔር ብለን ለመጥራት የሚያበቃን ምክንያት አለን ፤ አሁን በጀመርነው ዓመትም እግዚአብሔር የሚፈጽመው ለእኛ ብዙ ሥራ ስላለው ዓመተ እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ዓመት የምሕረት ዓመት ብለን ልንጠራው እንችላለን ።

ምንም እንኳን ባለፈው ዕድሜያችን በሠራነው ሥራ እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተነዋል ወደፊትም ሕጉን ትእዛዙን በሙሉ ፈጽመን ደስ ልናሰኘው እንችላለን ብለን ለመናገር ባንችልም በሃይማኖት ፤ በፍቅር ፤ በተስፋ ወደመሐሪነቱ መቅረብና ከከሀሊነቱ የሚፈልቀውን የይቅርታና የቸርነት ምጽዋት ለመቀበል መዘጋጀት ይገባናል።

እርግጥ እግዚአብሔር ከዚህ በፊት የሰጠኝን ጸጋ የተቀበልነው ወደፊትም የሚሰጠኝን የማይቋረጠውን ጸጋውን የምንቀበለው በዋጋ ለውጥ አይደለም ፤ ቢሆንም በሃይማኖት ፍጹም ታዛዥነት ይፈልግብናል ፤ ኃያል እግዚአብሔር ለሀልዎቱ የሥነ ፍጥረት ምስክር አለው ፤ ዝናምን ያዘንማል ፤ የተዘራውን ያበቅላል ፤ ያከርማል ያበጋል ፤ ፀሐይን ያወጣል ፤ ለአበባ ፤ ለፍሬ ያደርሳል ፤ የተራበውን ሰውነት ያጠግባል ፤ ያዘነውን ልብ ደስ ያሰኛል ፤ በዚህ ሁሉ ፍቅሩን ፤ ርኅራኄው ፤ ከሃሊነቱን ፤ ጌትነቱን ይገልጣል ፤ ግን ሰዎች ይህን ሁሉ እያዩ በሃይማኖት ባይጸኑ ፤ ትእዛዙን ባይጠብቁ ፤ ሥርዓቱን ቢተላለፉ ፤ መልካም ምግባር ቢያጠፉ በእምቢተኝነት ወደማይገባቸው ቢሄዱ ፤ ለስሙ ያዘጋጀውን ምስክር ሳይለውጥ ይተዋቸዋል ፤ በረድኤት ይለያቸዋል ፤ ያገባሉ ፤ ይጋባሉ ፤ ደስታ የላቸውም ፤ ይወልዳሉ ፤ ይራባሉ ፤ አይባረክላቸውም ፤ ይዘልሉ ፤ ያመርታሉ ፤ ነግደው ያተርፋሉ ፤ አይባረክላቸውም ፤ ኋላም ጽኑ ፍርድ ይጠብቃቸዋል ።

ሃይማኖታቸውን ቢያጸኑ ፤ ምግባራቸውን ቢያቀኑ ፤ ያዘዛቸውን ቢጠብቁ ፣ የከለከላቸውን እንዳያደርጉ ቢጠነቀቁ ፤ ስሙን ቢፈሩ ፤ አምልኮቱን ቢያከብሩ ፣ ለጊዜያዊ ነገር ባይሸነፉ ፣ ነባር ዓላማቸውን ለማጽናት ቢሰለፉ ፤ በኑሯቸው ደስ ይላቸዋል ። የወለዱት ፤ የዘሩት ፤ የተከሉት ይባረክላቸዋል ። ኋላም የማያልፍ ሕይወት የማይጠፋ ደስታ አላቸው ።

ዕድሜ እንዲጨመርልን እንወዳለን ። በያመቱ በዚህ ቀን የዘመን መለወጫን ስናከብር ደስ ይለናል ። ግን ሃይማንትን ከምግባር አስማምተን ለራስ ለሀገር ለወገን የሚጠቅም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ካልሠራንበት በየቀኑ የሚጨመርልን ዕድሜ መፈራረጃ ይሆንብናል ። የዕድሜ ጭማሪ የሚለካው በዓመቱ አይደለም ሰዓቱም ዕለቱም ወሩም በተጨማሪ የተሰጠን ታላቅ ጸጋ ነው ። ስለዚህ ሰው ለከንቱ ነገር የተፈጠረ አይደለምና እንደ አልባሌ ነገር እንደ ቀላል ዕቃም ወድቆ የሚቀር አይደለምና ከሞት ተነሥቶ ወደሌላ ዓለም ተ ውሮ ቅጣትና ክብር የሚጠብቀው ነውና ዕድሜውን በዋዛ ሊመለከተው ያለአንድ ዓላማ ሊያሳልፈው አይገባውም ።

እንደምታውቁት በአሁኑ ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ ብዙ ትግል ይታያል ዓለም የርሱ የሆኑትን ሲቀበል ቃላቸውንም ሲሰማ ቅእዛዛቸውንም ሲጠብቅ እኛ ግን የእግዚአብሔር ስለሆን ቃላችንን አይሰማም ። ዮሐ ፬ ፮ ። ግን አልሰማንም ብለን ዝም አንልም እንዲያውም ይህ ሁኔታ የእግዚአብሔር መሆናችንን ስለሚያረጋግጥ ልባችን በተስፋ ይጸናል ።

ሆኖም ዓለም ከነቤተ ሰቦቹ ወደ ተስፋ ሃይማኖቱ የሚገባበትን ፤ የገቡትም ወደ ሜዳ የማይወጡበትን ፤ የሕይወት መሰማርያ የሚያገኙበትን መንገድ በመሻት በብዙ በኩል መሞከር ይገባናል ። ሙከራችን በሁለት መስመር የተከፈለ ሆኖ ወላጆችንም ልጆችንም የሚመለከት ይሆናል ፤ ወላጆች ታሪክን መለስ ብለው ሊያስታውሱና ነባር ታሪክና ርስት ከባለታሪኮች መውረሳቸውን አስበው በዚያው አንፃር ለልጆቻቸው ማውረስ እንደሚገባቸው ሊገነዘቡት ይገባል ።

የሀገሩን የታሪክ ቅርስ ለልጆች ሳያስጠና ርስቱን ብቻ የሚያወርስ አባት በታሪክ ፊት መልካም ሥራ አልሠራም ማለት ነው ፤ ልጆችም ደግሞ ሥልጣኔ በመጀመሪያ የምታስተምረው ራስን ማወቅን እንደሆነ ሊረዱት ይገባል ፤ ራሳቸውን ካወቁ የነማን መሆናቸውን ከተረዱ በሥጋዊ በመንፈሳዊም ዓላማቸውን ጠብቀው ሊኖሩ ይችላሉ ፤ ራሱን የማያውቅ ሕዝብ ለታሪኩ የማይጠነቀቅ ትውልድ በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ታሪክ ገጽ ቦታ የለውም ፣ ቤተ ክርስቲያን እንደ መጻሕፍት ሕግ ፤ እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ በአርባ ቀን በሰማንያ ቀን እያጠመቀች ሥጋውን ደሙን እያቀበለች የልጅነት መብት ፤ የልጅነት ክብር ያለው የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ መሆኑን እያስተማረች ታሳድጋለች ፤ ከዚህ በኋላ ራሱ ክብሩን ንቆ መብቱን ጠልቶ ተዋርዶ ቢገኝ ራሱን አላወቀም ፤ ታሪኩንም አልተረዳም ማለት ነው ፤ ይህም ተምርን እንዳልተማሩ ያህል ያስወቅሳል ፣ ስለዚህ ወላጆችም ልጆችም ምክንያት ሳይፈጥሩ ራሳቸውን ሊቆጣጠሩ ይገባቸዋል ።

የክረምት ጐርፍ የማያመጣው ነገር የለውም ፤ በሀገር ያልነበረ ከውጭ የሚመጣ ነገር ሁሉ ወደ አገር ሲገባ የጥቅሙን ያህል ጉዳት የሚያስከትል ብዙ ነገር ማምጣቱ የታወቀ ነው ፣ ግን ተቀባዩ ወገን ሊጠነቀቅ ያሻል ፤ ኢትዮጵያ ለትውልድ ያወረሰችው ሁሉ በሥጋዊም በመንፈሳዊም ቢሆን የሚናቅ ነገር የለውም ፤ ስለዚህ አዲሱ ትውልድ እግሩን ከመንፈሳዊ ዓላማ ፈቀቅ እንዳያደርግ መጠንቀቅ አለበት ፤ የዛሬው በዓላችን ነባር መምህር ሆኖ ብዙ ትምህርት ይሰጠናል ፤ እንዲሁም ነባር መጽሐፍ ሆኖ ብዙ ምሥጢር ያቀርብልናል ፤ በመምህርነቱ ትምህርቱን እንስማው ፤ በመጽሐፍትነቱም ገስጥ አድርገን እንመልከተው ፤ አንድ ታላቅ አገርና አንድ ነባር ቤተ ክርስቲያንን አጣምሮ የያዘ ታሪክ ካላቸው ሕዝቦች መካከል ኢትዮጵያውያን መሆናቸው እርግጥ ነው ።

አባቶቻችን አገራቸውን ከቤተ ክርስቲያናቸው ሳይለዩ አስተባብረው ጠብቀው የኖሩ ይህን ዘመን የማይሽረውን በሰማይም በምድርም ፍጹም ዋጋ ያለውን ጎልፈት ውላጤ የማይስማማውን ታሪክ ስላወቁና ስለተረዱ ነው ። እኛም የነዚያ የቅዱሳን አበው ልጆች መሆናችንን ከመን የታሪካችንን ባለዋጋነት ልንገነዘብ ይገባናል ።

ዛሬ ይህን አዲሱን ዓመት በአሮጌ ሰውነት ሳይሆን በንስሐ በታጠበና በታደሰ ሰውነት ብንቀበለው በዓላችን እጥፍ ደስታን ይዞልን ይመጣል ።



www.ethiopianorthodox.org

ነገር ግን ከመካከላችን ገና በበግና በዶሮ መልክ የሚሟረቱና የሚያመልኩ እንዳሉ እንሰማለን በዚህ ሁኔታ የሚከበረው በዓል እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል ብለን እናስባለን ዕእናስብም ።

እንዲሁም በዳኝነት ወንበር ተቀምጠው መማለጃ ተቀብለው የሰው ፊት አይተው የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚያጣምሙ ደሀውን ባይተዋሩን የሚያጠቁ አይታጡም ይህ እያለ ባዓሉን በኅብረት በሙሉ ደስታ ማክበር እንችላለን ? በልዩ ልዩ ምክንያት በዓሉ የለቅሶና የኃዘን በዓል የሆነባቸው ስንቱ አሉ ? ብዙዎቹ በልተው ጠግበው ጠጥተው ረክተው ከዘመድ ከወዳጅ ተገናኝተው ደስ ብሏቸው ሲዝናኑ ከራሳቸው በላይ የቤት ጣራ የሌላቸው የበጋ ፀሐይ ያከሰላቸው የክረምት ዝናም ያለቀባቸው በረኃብ በእርዛቱ በችግር በሕማም በደዌ ተጨንቀው የበዓሉን ቀን በብዙ ችግር የሚያሳልፉት ወገኖቻችን ስንት ናቸው ? በመላው ዓለም በጦርነት በውሀ በጥልቅልቅና በልዩ ልዩ ፈተና የተፈተኑና የሞቱ የተሰደዱ ቤት ንብረታቸው ተፈትቶ ዓለም ጨለማ ኑሮ ፃዕር የሆነባቸው ዛሬ እኛ በዓል አድርገን ደስ ሲለን የሚያለቅሱ የሚያዝኑ የሚሠቃዩ ስንት ናቸው ?

ወገናችን የሆነው የሰው ልጅ ከጎረቤታችን ጀምሮ እስከ ጽንፈ ምድር ድረስ በልዩ ልዩ ችግር ተይዞ መሠቃየቱን በየጊዜው ስለምንሰማ በዓሉ የጥቂቶች ብቻ ሳይሆን የሁሉም ይሆን ዘንድ በተፈጥሮ ለሚመስለን ሁሉ የርኅራኄና የፍቅር ሥራ ልንሠራለት በሩቅም በቅርብም በባሕርም በየብስም ላሉ ሁሉ ልናገዝላቸውና በጸሎትም ልናስባቸው ይገባል ። ይህንን ብናደርግ በንስሐም በንመለስ ግን «ብፁዓን መሐርያን እስመ ሎሙ ይምሕርዎሙ»ያለው እንዴት ሊፈጸምልን ይችላል ? ሁሉን ማድረግ የሚቻለው ልዑል እግዚአብሔር አዲሱን ዓመት በንሰሐ ታድሰን በአዲስ ሰውነት ለመቀበል በአዲስ መንፈስ ተነሣስተን የጽድቅ የርኅራኄና የፍቅር ሥራ ለመሥራት ያብቃን ።

ሀገራችን ኢትዮጵያን ከእግዚአብሔር መዓት ሕዝቡን ከመቅሠፍት ወገኖቻችንን ከስደት ይሰውርልን ንጉሠ ነገሥታችንን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ረጅም ወራት ሰፊ ዘመናት ሰጥቶ በጽኑ ሥልጣኑ ይጠብቅልን ። ወራሴ መንግሥቱን ልዑላንና ልዑላት አገዛዛ መንግሥቱን ይባርክ ። ለመላው ዓለም ሰላምን ሥልጣን ላላቸውም ማስተዋልን መስማማትን ያድልልን አዲሱን ዓመት ዘመነ ማቴዎስን ዘመነ ሰላም ዘመነ ሣህል ያድርግልን ሁሉንም በያለበት እያንዳንዱን ወደ ጽድቅ ወደ ፍቅር ወደ ሃይማኖትና ወደ በጎ ምግባር እንዲመራ ጸጋውን ያድልልን በዓሉን የደስታ በዓል ያድርግን ። አሜን ።



# የሰላም ልደት
# በአፍሪቃ ፤

ከቀሲስ ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ በኢጀርሳ ጎሮ እግዚአብሔር ከቀደሰው ማኅፀን እንደ ጧት ጮራ በ፲፰፻፹፬ ዓ ም ሐምሌ ፲፮ ቀን የእግዚአብሔርን ረድኤት ተጐናጽፈው ብቅ ሲሉ ኢቶዮጵያ ብቻ ሳትሆን መላዋ አፍሪቃ ሰላም ተወለደላት ። በቅኝ አገዛዝ ሥር ወድቃ የነበረች የሰላምን ጸጋ የተገፈፈች አፍሪቃ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ልደት ሰላምን ፤ ፍቅርን ፤ አድነትን ፤ አገኘች ። የዚህም ትርጉም ተገልጾ መላዋ አፍሪቃ የጃንሆይን ፹ኛ ዓመት የልደት በዓል የሰላም ዓለቃ ብላ በታላቅ አንክሮ አክብረዋለች ።

የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ልደት ከፍጡራን ከማን ልደት ጋር ይመሳሰላል ? ቤተ ክርስቲያን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መንፈሳዊ አሠረ ጽድቅ ተከትሉ በእርሱ ቡራኬና ጸጋ የተሰጠ ልዩ የሰላም ፤ የፍቅር ፤ የአንድነት ልደት ፤ ብላ ትሰይመዋለች በሥጋዊ የታሪክ መሥመር አፍሪቃና መላው ዓለም ወደር በማይገኝለት ቃል የጃንሆይን ታሪክ በሰፊው ይተርካሉ ፤ አድናቆታቸውን ይገልጻሉ ። ቤተ ክርስቲያን ስለጃንሆይ መንፈሳዊነትና ስለፈጸሙላት መልካም ወሮታ ምን አስተያየት አላት ? መሠረታዊቷ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ከነገሡት ነገሥታት የበለጠ ፍቅር መንፈሳዊ ፤ አስተያየትና አመለካከት አላት ።

<u>ይህንንም በመጠኑ ለማስታወስ ያህል</u>

፩ኛ ጃንሆይ በአምላካችን በጎ ፈቃድ ለኢትዮጵያ ፤ ለአፍሪቃና ለመላው ዓለም ሰላም የተፈጠሩት ፈሪሃ እግዚአብሔር ካለው ፤ ከሃይማኖተኛው ፤ ለእግዚአብሔርና በዘመኑ ለነበረው ለዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፤ ለኢትዮጵያም ታማኝ ከሆነው ከልዑል ራስ መኰንን የተቀደሰ አብራክ ተከፍለው መንፈስ ቅዱስ ከባረከው ከክብርት ወይዘሮ የሺ እመቤት ማኅፀን ተወለዱ ፤ በተወለዱ በ፵ ዕለታቸው ጌታቸው መድኃኒታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በ፵ ቀኑ ሕገ ኦሪትን ለመፈጸም ወደ ቤተ መቅደስ ሰጉለ ርግብ ፤ ዘውገ ማዕነቅ ይዞ ገባ ።

ግርማዊ ጃንሆይም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የጽድቅ አሠረ ፍኖት በሚከተሉ ቤተ ሰቦቻቸው ታጅበው አምኃ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ሐዲስ ሥርዓት ይዘው ፀሐረር ወደሚገኘው የኮምቦልቻ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሔደዋል ። ነቢዩ ስምዖን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እጁን ዘርግቶ በደስታ ተቀብሎ አቅፎ «ጌታ ሆይ አሁን እንደቃልህ ባርያህን ታሰናብተዋለህ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብም ለእሥራኤል ክብር ነው ሉቃስ ፪ ፳፱—፴፪ ብሎ በትንቢት እንደተናገረው ሁሉ የኢትዮ



www.ethiopianorthodox.org

ድያ ቤተ ክርስቲያን ካህናትም በዚያን ጊዜ የዛሬ ፺ ዓመት ተወልዶ ስመ ክርስትናን ሀብተ ወልድናን በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለማግኘቅ በሃይማኖታውያን ወላጆቹ ክንድ ወደቅድስት የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የመጣውን ሕፃን በታላቅ አክብሮት ተቀብለው በስምያን ትንቢት አንፃር እየተመለከቱት ጸዋ ባለ መንፈሳዊ መንፈስ ጸልየው ስመ ክርስትናውን ኃይለ ሥላሴ ብለው ሠይመውታል ፡፡

ግርማዊነታቸው በተወለዱ በ፵ ቀናቸው በጥምቀተ ክርሰትና ልጅነትን ሲቀበሉ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተሰጣቸው « ኃይለ ሥላሴ » የሚለው የስመ ክርስትና ተጸውዖ የሥላሴ ኃይልና ጽንዕ በላያቸው አድሮ ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያን እንዲጠብቅ ፤ ለመላዋ አፍሪካና ለዓለምም እንዲተርፍ መንፈስ ቅዱስ የገለጠላቸው ቅዱሳን አበው ካህናተ ቤተ ክርስቲያን ከወላጆቻቸው ጋር በመስማማት እንደሰየሙት መንፈሳዊ ታሪክ በጉልህ ያስረዳል ፡፡

የሀብተ ወልድና የስመ ክርስትና ስሙ « ኃይለ ሥላሴ » በዓለም ስሙ ግን «ተፈሪ መኰንን» ተብሎ የተሰየመው ብሩህ ገጽ ወልብ የሆነው ሕፃን በመንፈሳዊ በዓላት ሁሉ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበለ አደገ ። የሕፃኑ እድገት በቁመተ ሥጋ ብቻ ሳይሆን በሥጋዊና በመንፈሳዊ ጥበባት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት ያድግ ነበር ። አስተዳደጉ አዳኙንና መድኃኒቱን ኢየሱስ ክርስቶስን የተከተለ ነበር ፡፡

በመዋዕለ ውርዝውናው ቀን ሕገ ቤተ መንግሥትንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በጥንቃቄ እየተማረ ፤ በዕለተ ሰንበትና በየበዓላቱ ዕለት በመንፈቀ ሌሊት ከሞግዚቶቹና ከቤተ ክርስቲያን ካህናት ጋር በቤተ ክርስቲያን በመገኘት ጸሎተ ሰዓታት ሲደረስ አብሮ እየጸለየ ያድር እንደነበረ በዘመኑ የነበሩ አረጋውያን ካህናት ይመሰክራሉ ፤

ነቢዩ ሣሙኤልን በሕፃንነቱ ጽላተ ሕግ ታቦተ ኪዳን ከምትገኝበት ደብተራ ኦሪት በመንፈቀ ሌሊት ለእሥራኤል ሕዝብ መሪነት ይበቃ ዘንድ መመረጡን ሲነግረው የጠራው የእግዚአብር መለከታዊ ቃል ሕፃን ኃይለ ሥላሴን በደሙ በዋጃት ቅድስት ቤተ ክርስቲያኑ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መሪነት ለአፍሪቃ ሕዝብና ለመላው ዓለምም አንድነት እንደጠራው ግልጽ ነው ።

በቁመት ፤ በጥበብ ፤ በመንፈስ እያደገ የሔደው ተፈሪ መኰንን « የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው » ተብሎ በብልሁ አባቱ በንጉሠ ነገሥት ሰሎሞን የተጻፈውን ቃል ከልብ የጠበቀ ሆኖ ከፍ ከፍ ይል ጀመር ፤ ፍጹም መንፈሳዊ ከሆነ ቤተሰቡ በወረሰውና ከልብ በአመነበት የኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት በጾም ፤ በጸሎት ፤ በምጽዋቅ በልዩ ልዩ ቱሩፋት ሰውነቱን አንጾታል ።

ልጅ ተፈሪ መኰንን ይባል የነበረው ጉብል (ሕፃን) ፲፬ ዓመት ሲሞላው በጀግና አባቱ መልካም ፈቃድ ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን ተባለ ። በመንፈሳዊ አባቱ የተሰጠው ማዕርግ በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ጸደቀ አንተነቱ ወደ እርስዎነት ተለወጠ ፡፡ በነቢዩ ሙሴ ፃጽ ላይ እግዚአብሔር አምላክ ብርሃናዊ ግርማ



ሞገስን እንደሳለ ፤ በእሥራኤል ሕዝብ ዘንድ መወደድንም እንደሰጠ ሁሉ ለክቡር ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን «ኃይለ ሥላሴ» ተብለው በስመ ክርስትና በሀብተ ወልድና በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም የታተሙ ዕለት ግርማ ሞገስን ፍቅርን በሕዝባቸው ዘንድ መወደድን ስለ ሳለባቸው በትልቁም በትንሹም ዘንድ ያላቸው ፍቅር እየሞቀ እየጋለ ሄደ፤

የክቡር ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን ልቡና የለሰለሰ ገራኅተ ጽድቅ ( የጽድቅ እርሻ ስለሆነ) የሃይማኖት ፤ የፍቅር የተስፋ ፤ የትሕትና የትዕግሥት ፤ የቸርነትን ጥዑም ፍሬን አፈራ ። ጥዑም ፍሬውም ወደኢትዮጵያ ሕዝብ አደባባይ ወጣ ሁሉም ጎመጀው ሥርወ መንግሥቱ ንጉሥ ዳዊት የሆነው ክቡር ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን በአዛውንቱ በመኳንንቱ ፤ በወይዛዝሩ ፤ ከፍ ብሎም በንጉሠ ነገሥቱና በእቴጌይቱ የተደነቁ ሆኑ ።

ከዚህ ላይ የሩቅ ምሥራቅ ንጉሠ ነገሥት የነበረ የታላቁን ጴጥሮስን ታሪክ በአንፃር ልናወሳ ይገባል ፤ ታላቁ ጴጥሮስ ካለፈ ከብዙ ዓመታት በኋላ የተወለደው ፑሽኪን በቅኔው ያወሳውን እናነጻጽር ዘንድ ይገባል ።

የኢትዮጵያዊው አብርሃም የልጅ ልጅ አሌክሳንደር ፑሽኪን የታላቁ ጴጥሮስ ሥራ አስደንቆት በቅኔው ሲያወሳ እንዲህ አለ « ማዕበል በሚፈንጭበት ኒባ ከሚባለው ታላቅ ጅረቅ ዳር ታላቁ ጴጥሮስ ቆሞ ወደባሕሩ መከከል ሲመለከት እጅግ በጣም ቅንሽና አሮጌ ጀልባ ቡቶቶ የለበሰ ድኃ ተቀምጦ እየቀዘፈ በዝግታ ወደባሕሩ ዳርቻ ሲመጣ ታላቁ ጴጥሮስ ተመልክቶ ጥቂት ከአሰበና ከተከዘ በኋላ በዚህ ታላቅ ጅረት ዳር በጣም ታላቅ ከተማ ይቆረቆራል በዚህ ባሕር ላይ የአውሮፓ መስኮቶች ይከፈታሉ ፤ በጣም ታላላቆች መርከቦች ወደእዚህ ይመጣሉ ፤ በዚህ ሥፍራ የዓለማት ሰንደቅ ዓላማዎች ይተከላሉ የዓለም መሪዎች ይሰበሰባሉ ፤ በአንድነትም ሆነን በቁም ነገር እንጫወታለን አለ ፤ ታላቁ ጴጥሮስ ያሰበውና የተናገረው ተፈጸመ» ብሎ በታሪክ መነጽርነት ያለውን ተመልክቶ በዘመኑ ለነበሩት አድናቆቱን በቅ◌ነው አማካይነት ገልጿል ፡፡

የዚያን ጊዜው ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን የዛሬው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሰ በሕፃንነታቸው ጊዜ ከታላቁ አባታቸው ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ ጋር በታላቁ ቤተ መንግሥት አደባባይ ሲመላለሱ የኢትዮጵያን እድገትና መሻሻል የአፍሪቃን የሰላም ዕድል በአእምሮአቸው ቸር እግዚአብሔር ስሉ ያሳያቸው እንደነበር ዛሬ በደረስንበት የዓይን ምስክርነት ስንመለከቅ እንደ ፑሽኪን ልንመሰክር ችለናል በቅኔያቸው የመሰከሩም ብዙዎች ናቸው ።

እነሆ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥቅ የአውሮፓ የሥልጣኔ በር ተከፈተ የአሰብ ወደብ ተስፋፍቶ ተሠራ ፤ ብዙዎች ታላላቅ መርከቦች ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ።

የዓለም መንግሥታት ሠንደቅ ዓላማ በዓንድነት ሆኖ በአዲስ አበባ አውለበለበ የመላዋ አፍሪቃ ሰንደቅ ዓላማ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በተመሠረተው የአፍሪቃ አዳራሽ አንድነቱን ገለጸ ፡ ቀድሞ በኢትዮጵያና እንዲሁም በአፍሪቃ ያልነበረው



www.ethiopianorthodox.org

ታየ ። ያልተደረገው ተደረገ ፤ ይፀን ሁሉ የኢትዮጵያና የአፍሪቃ ትውልድ በታሪክ ትዝታ ወደኋላ ሲያስብ ለአሌክሳንደር ፑሽኪን የታላቁ ጴጥሮስ ሥራና ታሪክ እንደ ብርሃን ወጋገን እንደተገለጸለት ሁሉ በአሁኑ ዘመን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በጎ ዓላማና ሥራ በ፹ ዓመት ዕድሜ ፃፍ ላይ አፍርቶ ታይቶታል መላዋ አፍሪቃ የምሥጋና ቅኔ ትቀኛለች ፤ መላው ዓለምም አድናቆትንና አክብሮቱን ይገልጻል ።

ኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲያናችን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ወራሴመንግሥት ዘኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሲባሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መሪ ሆነው የተገኙበትን ሰማንያኛውን በዓለ ልደታቸውን ስታከብር በታላቅ አድናቆቅ ታስታውሰዋለች ።

በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሥርዓተ ንግሡ ላይ « እመሰ ጾምከ ወጸለይከ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ትጸውር በዝግና ወርቅ ውስተ ክሣድከ ፤ አክሊለ ክብር ዲበ ርእስከ በጽርሐ ቅድሳቱ ለምኒልክ ሶበ ይኤምኑከ ጳጳሳት » ብለው ካህናተ እግዚአብሔር የዘመሩት ግሥ በታላቅ መንፈሳዊ ስሜት በቤተ ክርስቲያን ዓምድ ተቀርጾ ይታያል ። ከልጅነታቸው ጀምሮ ከቤተ ክርስቲያን በተማሩት ከወላጅ አባታቸውና ከዳግማዊ ምኒልክ በአገኙት በተለይም ከእግዚአብሔር ልዩ ሀብት ሆኖ ስለተሰጣቸው ጾምና ጸሎት ገንዘባቸው ስለሆነ እንሆ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውዳቸውን እንደጫኑ የሰማንያኛ በዓለ ልደታቸው በሰላም ደረሱ ።

ንጉሠ ነገሥት በተፀለሉበት ቀን በቤተ ክርስቲያናቸው ከሰሙት ቃለ ዓዋጅ «ሳናስበው ፈጣሪያችን በሕዝቡ አድሮ መርጦን እንዳናገረው ዓዋጅ የእናትና የልጅ ቃል ኪዳናችን ሳይፈርስ በእርሱ ሕግና ትእዛዝ ሆኖ ከመሬቅ የሚቀር የለምና በጥቂት ቀን ሕጣም ስለአረፉና ስለተቀዳደምን ምንም የግርማዊቅ ንግሥተ ነገሥታት ማለፍ ለእኔም ለመላው ኢትዮጵያም ኃዘናችን ቢሆን የሕዝቡ እረኛ ንጉሥ ሲሞት ንጉሥ መተካቱ የቆየ ልማድ ስላሆነ እኔም በታጭሁበት መንበረ ዳዊት ሆኜ በእግዚአብሔር ቸርነት እጠብቅሃለሁና ፤ ነጋዴም ነግድ ገበሬም እረስ ከባቶቹ ሲያያዝ በወጣው ሕግና ደንብ አሳድርሃለሁ ብለዋል» ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ይህን የቃል ኪዳን ንጉሣዊ ቃል ለሕዝባቸው ያሰሙት ቅብዓ መንግሥት ተቀብተው በነገሡበቅ ወቅት ቅድስት ቤተ ክርስቲያያንን ምሥክር አድርገው የተናገሩት ነበር ።

እምልተውና አስፍተው ሕዝባቸውን ጠባቂ ፣ ረዳ እንጂ ምንም የጎደለ ነገር አለመኖሩን ቤተ ክርስቲያን ምስክርነቷን ትሰጣለች ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በመናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ንግሡ ሲፈጸም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከገቡት ቃልኪዳን አንዱ የመጀመሪያው ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ለተዋሕዶ ሃይማኖቷ የገቡት ቃል ኪዳን ነው ።

ሊቀ ጳጳሳቱ ሲጠይቋቸው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥቅ ሆይ እንደ ነገሥታት ደንብ ሲነግሡ ሊደረግ የሚገባውን መሐላ ይፈቅዳሉን ።



አዎን እፈቅዳለሁ ።

ከቅዱሳን ነገሥታት (ከአብርሃ አጽብሃ) ጀምሮ በኢትዮጵያ ጸንቶ የኖረውን የእስክንድርያ የኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የወሰነችውን ሕግና ሥርዓት ባለማፍረስ ለመጠበቅ ይምሉ ዘንድ ይፈቅዳሉን ።?

የአስክንድርያን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እስካሁን እምኜበት የምኖር ነውና ወደፊትም በእግዚአብሔር ርዳታ ጠብቄ እንድኖር ለመማል ፈቃዴ ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያን ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ አሻሽለውታል ወራሴ መንግሥት በነበሩበት ጊዜ በግል ገንዘባቸው ዘመናዊ ማተሚያ ቤት አቋቁመው መጻሕፍት ቅዱሳት በቅድሚያ እንዲታተሙ በማድረግ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷ እንዲሻሻል አድርገዋል ።

እንኳን ንጉሠ ነገሥት ሆነው ገና አልጋ ወራሽ ሳሉ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጽጽስናን ማዕርግ አሰጥተዋል ፤ በታላቅ ቃል ኪዳን ተቀብተው ንጉሠ ነገሥት ከተባሉ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዕድል ከኢትዮጵያ ጋር እያደገ ከፍ ከፍ እያለ ሄደ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በመንፈስ ቅዱስ እየተቃኙ የኢትዮጵያና የቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድል በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሆኑ እየታያቸው ገና ሳይነግሡ ትንቢታዊ ቅኔ ይቀኙ ነበር ። ስለዚህም

አለቃ አርአያ ወረታ በሐረር መከነ ሥላሴ የተቀኙት ትንቢታዊ መወድስ ቅኔ እንዲህ የሚል ነበር ።

ኃይለ ሥላሴ ኢታንክር እመ አቤለከ
ርኢኩከ አንሰ ታሕተ ዕፀ ሐረር ዓባይ
ሀለወከ ትዕርግ መንበረ ምኒልክ ሰማይ
ወብከ ዘተሐቱ ዘዕንቀኑ መንግሥተ አቡከ ሰሎሞን ባሕርይ ።
መከነ ሥላሴሰ ትሴሰይ ዘትረ ግብረ መድኅን መዓር
ሥውጠ አንከር ሥርናይ
ሊተኒ ያሠጥመኒ ዕመቀ ፍሥሐ ቀላይ
እግዚ ቃለ ፍትሕከ እሰምእ በዓውደ ምኒልክ ደብረ ምስካይ
እስመ ከመ በግዕ የዋህ ወከመ ተኩላ ዕቡይ
ጎቡረ ይቅረአዩ ባዕል ወነዳይ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የተነገረው ትንቢት ተፈጸመ ፤ ወራሴ መንግሥት ንጉሥ ተፈሪ ንጉሠ ነገሥት ሆነው ተቀቡ ፤ ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያና ቤተ ክርስቲያናችን የተቃና የዕድገት መርሐ ፍናት ተከፈተላ



www.ethiopianorthodox.org

ቸው ፤ ጠላት ቅድስት አገራችን ኢትዮጵያን በግፍ በወረረ ጊዜ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር የጠላትን ግፍ ለመግለጽ ሔደው ስለ ቤተ ክርስቲያን አልተለየቻቸውም ፤ የመድኃኔ ዓለም ጽላት ፤ ታቦተ ሕግና ክህናት አብረዋቸው በለንደን ከተማ ነበሩ ፤ የነግህ ፤ የሠርክ ፤ የሌሊት ጸሎትና ምሕላ አልተጓደለም ፤ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በየዕለቱና በየሰዓቱ አብረዋቸው ይጸልዩ ነበር ፤ ጸሎተ ቅዳሴውም በሚገባ ይከሄድ ነበር ፤ በዚያን ጊዜ አብሮአቸው የነበረው ታቦት አሁን በአዲስ አበባ ከተማ ግርማዊነታቸው በጣም ደስ የሚያሰኝ ቤተ ክርስቲያን ያሳነጹለት ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ነበር ፤

ይህን ጽላት ጃንሆይ ወደለንደን ከማስወሰዳቸው በፊት ለብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ከጻፉት መልእክት ውስጥ እንዲህ የሚል መልእክት ይነበባል « የእግዚአብሔር ቸርነት ፈቅዶልናልና አሰናብቶን ወደ ኢየሩሳሌም እስከምንመጣበት ቀን ድረስ የሃይማኖት ችግር እንዳያገኘን የሚያድጉትም ልጆቻችን የሃይማኖታቸውን መሠረት እንዳያጡት አስበን እንድጽላትና አምቢት መነኮሳት የሚያስፈልጉትን ንዋየ ቅድሳትና መጻሕፍት ሰጥተውት ይዞ እንዲመጣ አባ ሐናን ልኬዋለሁና ከመምህር ገሪማ ጋር ተመካክራችሁ አቢይ ጾም ሳይገባ እንዲደርስ አድርጋችሁ እንድትልኩልን ይሁን» የሚል ነበር ፤ በንጉሣዊ መልእክት መሠረት ተፈጸመ ፤ የተጸለየው ጸሎት የተሠዋው መሥዋዕት ቅድመ እግዚአብሔር ደርሶ የኢትዮጵያ ነፃነት ተመለሰ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት ከመናገሻ ከተማቸው አዲስ አበባ እንደገቡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር አምላካቸው የሚመሰገንበትን ቤተ ክርስቲያን ሁሉ በየሥፍራው እንዲታደስ አደረጉ ። ለችግረኞች ካህናት ፤ ምእመናን ርስት ፤ ገንዘብ ልብስ ከብት በመስጠት የጠፋ ንብረታቸውን አቋቋሙላቸው ።

ወዲያውኑ በ፲፱፻፴፬ ዓ. ም. መጋቢት ፩ ቀን ፤

፩· ስለ ቤተ ክርስቲያን ርስት ዝርዝር ፤
፪· በቤተ ክህነት ርስት ስለሚከፈለው ግብር ፤
፫· ለቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ስለተሰጣት ጉልት ፤
፬· ስለየበዙኛ ጉልት ገቢ ገንዘብ ፤
፭· ስለገበዞች ፤
፮· ስለ ካህናት አስተዳደር ፤
፯· ስለ ቀለብ ውሳኔ ፤
፰· ስለ ቤተ ክርስቲያን ገንዘብና ሀብት ጥበቃ ፤
፱· ስለ ቤተ ክርስቲያን ርስትና ገንዘብ ጥበቃ ፤
፲· ስለ ዳኝነት ፤
፲፩· ስለ መንፈሳዊ ሹመት ፤
፲፪· ስለ አዲሱ ደንብ አቋቋም እንዲህ ሲሉ ደምብ አወጡላት ፤



# ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
# ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

## ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

በሕገ መንግሥታችን በ፲፩ኛው ቍጥር የተጻፈውን ተመልክተን የመንፈሳዊ ጉባኤ ስለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር መክሮ ያቀረበውን አሳብ ተመልክተንና ፈቅደን ስለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ከዚህ ጋር የተያያዘውን ደንብ ሰጥተናል ። መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ. ም. በአዲስ አበባ ከተማችን ተሰጠ ።

በ፲፱፻፴፭ ዓ. ም. ለብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ (በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ) ተመርጠው የቀረቡት ፳ (ሐያ) ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በቤተ መንግሥታቸው የእንግሊዝኛ ቋንቋን እንዲማሩ ፈቀዱ ። ገና ሲቀቡ ለመንፈሳዊ ዕድገቷ ቃል ኪዳን የገቡላት ቤተ ክርስቲያን በጣም ከፍ ከፍ እንድትል የዘወትር ምኞታቸው ስለ ነበር በቤተ መንግሥታቸው በሐያ ሊቃውንት የተወጠነው ዘመናዊ ትምህርቅ ሰፋ ይል ዘንድ በግል ገንዘባቸው የቅድስት ሥላሴን መንፈሳዊ ትምህርት ቤትን አሳነጹ ። የውጭ አገርና ብሔራውያን መምህራንን ቀጥረው መንፈሳዊና ጥበባዊ ትምህርት በሰፊው እንዲሰጥ አደረጉ ። በዚሁ ትምህርት ቤት የመምህራን ማሠልጠኛ እንዲቋቋም ስለተደረገ በአሁኑ ጊዜ በመላዋ ኢትዮጵያ የሥነ ምግባርና የሃይማኖት የአማርኛ ሰዋስው መምህራን ሆነው ያገለግላሉ ። መንፈሳዊው ት/ ቤቅ ወደ ኮሌጅ ደረጃ ደርሶ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ሕግ እየተዳደረ የቲዎሎጂ (የነገረ መለኮት) ሊቃውንትን በየዓመቱ ያስመርቃል ። በዚህ መንፈሳዊ ት/ ቤት ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ብዙዎች ወደ ውጭ አገር የተላኩ ወጣቶች እስከ ዶክተርነት ማዕርግ ደርሰው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰሮች ለመሆን በቅተዋል ። በልዩ ልዩ አስተዳደር ተሠማርተዋል ሁሉም የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፍሬዎች ናቸው ።

ከዚህስ በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለቤተ ክርስቲያን መሻሻልና እድገት ምን አደረጉ ? የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ታላቁ ሐሳብ ኢትዮጵያውያን ከሊቃውንቶቻቸው መካከል ጳጳሳትን አይሹሙ ተብሎ የአበው ሕግ በማስመሰል በተንኮል በፍትሐ ነገሥት የተጻፈውን ቃል በእውነት ቃል ሠርዞ ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ከልጆቿ ጳጳሳትን ሾማ ከእግዚአብሔር በረከትን እንዳታገኝ ነበር ።

ይህንም ሐሳብ በድል አድራጊነት ከተመለሱ በኋላ ወዲያውኑ በ፲፱፻፴፬ ዓ ም ከግብፃውያን ጳጳሳትና መምህራን ጋር በመነጋገር ወጡ ፤ በፍጹም ትዕግሥት ቀስቢለው ስለያዙት የእግዚአብሔርም ፈቃድ ስላሆነ በ፲፱፻፵ ዓ ም ሐምሌ ፲፰ ቀን እሑድ ካይሮ በሚገኘው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን

| | |
|---|---|
| ፩ኛ ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ | (አቡነ ባስልዮስ) |
| ፪ኛ መምህር ገሪማ | (አቡነ ሚካኤል) |



www.ethiopianorthodox.org

፫ኛ ሊቀ ሥልጣናት መልአክቱ — አቡነ ቴዎፍሎስ
፬ኛ መምህር ዘፈረ ብርሃን — አቡነ ያዕቆብ
፭ኛ መምህር ጌታሁን — አቡነ ጢሞቴዎስ

በመባል ጳጳሳት ሆነው ተሾሙ ።

የግርማዊ ንጉሠ ነገሥቅ መንፈሳዊ ሕሊና በዚህ ብቻ አልተገታም ። አገራቸው ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት እንድትመራ የሁል ጊዜ ምኞታቸው ስለነበር በትዕግሥት ከኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር መነጋገር ጀመሩ ፤ ቸር አምላክ ከግርማዊነታቸው ጋር ስለሆነ ሀሳባቸው ተቃና ብፁዕ አቡነ ባልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ተመርጠው ጥር ፯ ቀን እሑድ ፲፱፻፵፫ ዓ. ም. በግብፅ በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሆነው ተሾሙ ።

የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ረቂቅና መንፈሳዊ ሕሊና አሁንም የመጨረሻ የሆነ አንድ ነገር እንደቀረ ከማሰብ አልተወገደም ፤ ይኸውም አገራቸው የራሷ የግሏ የሆነ ፓትሪያርክ እንዲኖራት ማድረግ ነበር አሁንም ቀስ በቀስ በመንፈሳዊ ዘዴ መንፈሳዊ ርምጃቸውን ቀጥለው በመጨረሻው አስደናቂ የሆነ መንፈሳዊ ድልን በማግኘት ብፁዕ አቡነ ባልስዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሆነው እንዲመሩ ተመረጡ ። የጃንሆይ ሐሳብ ሰኔ ፳፩ ቀን ፶፩ ዓ ም በግብፅ በመንበረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተከናወነ ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ካረፉ በኋላ ግርማዊ ጃንሆይ እጅግ ከፍ ያለ የመጨረሻ መንፈሳዊ ዕድልና ድል ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስገኝተውላታል ። ይኸውም ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነጳጳሳት ፓትርያርክ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ሆነው በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ ክርስቲያን ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. መሾማቸው ነው ። ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የፈጸሙት መንፈሳዊ ታሪክ በሰማያዊ የወርቅ ቀለም ተጽፎ ለዘለዓለም ይኖራል ፤ ከእግዚአብሔር አምላካቸውም እጥፍ ድርብ ዘለዓለማዊና ሰማያዊ ክብር እንደሚያገኙ በት ቤተ ክርስቲያን ታምናለች ።



www.ethiopianorthodox.org